## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

### ንስሐ ምንድን ነው?

ንስሐ ማለት ነስሐ ተጸጸተ ካለው የግእዝ ቃል የወጣ ነው። በመሆኑም ንስሐ ማለት ጸጸት፣ ኀዘን፣ ቅጣት፣ ቀኖና ወዘተርፈ ማለት ነው።

ንስሐ አንድ ሰው በፈጸመው ኀጢአት ከአዘነና ከተጸጸተ በኋላ ዳግመኛ ወደዚያ ኃጢአት ላለመመለስ የሚደረግ ውሳኔም ነው በአመንዝራነት ኃጢአት ተከሳ በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ለነበረችው ሴት የተሰጠው ማስጠንቀቂያም ይሔው ነበር «ከአሁን ጀምሮ ዳግመኛ ኀጢአት አትሥሪ» ዮሐ.8÷11 ስለዚህ የንስሐ ትልቁ ትርጉም በሕይወት ላይ ሰፍኖ የነበረን ኀጢአት ማስወገድና ድጋሚ ወደዚያ ኃጢአት አለመመለስ ነው።

ንስሐ በኃጢአት ምክንያት የተጻፈን ልብ አጥርቶ የኃጢአት እንቅፋቶችን አስወግዶ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ ታላቅ መንፈሳዊ በረከት ነው።

ይህ ታላቅ በረከትም በነቢዩ ሕዝቅኤል የትንቢት መጽሐፍ እንዲህ ሲል ተገልጿል።

«እንቅፋትእንዳይሆንባችሁ ከኀጢአታችሁ ተመለሱ፣ የበደላችሁትን በደል ሁሉ ከእናንተ ጣሉ፣ አዲስ ልብና አዲስ መንፈስም ለእናንተ አድርጉ። ለምን ትሞታላችሁ የሚቹን ሞት አልፈቅድም ይላል ጌታ እግዚአብሔር ስለዚህ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ። ሕዝ.18÷30 የሰው ዘር በኃጢአት ከወደቀበት ጊዜ አንስቶ ከተሰጡት የድኅነት መንገዶች አንደኛው ንስሐ ነው።

ንስሐ የቦታና የጾታ ልዩነት ሳይደረግ የሚፈጸም ሥርዓት መሆኑን ቅዱሳት መጽሐፍት ይመክራሉ «እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል። የሐዋ.17÷30 በማለት የሰው ልጅ እግዚአብሔር ከአባትነት ፍቅሩ የተነሳ ያደረገለትን ቸርነት በመዘንጋት በኃጢአት ባርነት ተይዞባቸው የቆየባቸው ወራቶች ያለማወቅ ወራቶች ተብለዋል ምክንያቱም በታሪክ ተደጋግሞ እንደምናነበው አንድ ሰው ኃጢአት መሥራትን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ አእምሮው በአለማወቅ ጥቁር መጋረጃ ይሸፈናል። የሚፈጽመው በደል ሁሉ ለእርሱ መልካም እየሆነ ይታየዋል ለምሳሌ ታሪኩ በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 18÷1-34 የተመዘገበው የእሥራኤል ንጉሥ አክአብ እውነተኛውን ነቢየ እግዚአብሔር ሚክያስን ከመስማት ይልቅ አራት መቶ ነቢያተ ሐሰትን እንዲሰማና ምክራቸውን እንዲቀበል ያደረገው አእምሮውን የጋረደው ያለማወቅና ያለማስተዋል መጋረጃ እንደነበር እናስተውላለን።

ስለዚህ በየትኛውም ክፍለ ዓለም በሥራና በኑሮ ምክንያት የተለያዩ የሰው ልጆች በቦታው አቀማመጥ ይለያዩ እንጅ ኀጢአትን በመሥራት ተመሳሳይነት የሚታይባቸው ስለሆነ እነርሱ ባሉበት ሀገር እግዚአብሔር አለና በያሉበት ንስሐ ይገቡ ዘንድ መታዘዛቸውን ያስረዳል።

ንስሐ ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን አንዱ ነው የመሠረተውም መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ምንም እንኳን ከዘመነ ነቢያት ጀምሮ የሰው ልጆች ከበደላቸው ተመልሰው ንስሐ እንዲገቡ ቅዱሳት መጽሐፍት ተባብረው ቢመክሩም በወቅቱ የነበረው የንስሐ ውጤት ግን ገነት /መንግሥተ ሰማያት/ ለማስገባት ኃይል አልነበረውም። ምክንያቱም በአሪቱ ሰው ሁሉ በአዳም መርገም የተያዘ በመሆኑና ከዚህ መርገምም ሊያነፃው የሚችል ጽድቅ፣ ነፃ የሆነ ካህን ስላልነበረው ነው። ነቢዩ ኢሳይያስ «ሁላችን እንደ ርኩስ ሰው ሆነናል ጽድቃችንም ሁሉ እንደመርገም ጨርቅ ነው። ሁላችንም እንደቅጠል ረግፈናል በደላችንም እንደነፋስ ወስዶናል» ያለውም ይኸንኑ የሚያሳይ ነው። ኢሳ.64÷6፤ ዕብ.7÷26-28።

1. ንስሐ የመግባት ጥቅም በብሉይ ኪዳን

ሀ. የመጀመሪያው ሰው አዳም በጠላት ዲያብሎስ አስመሳይ ቃል ተታሎ የነበረበትን የክብር ቦታ የተሰጠውን ልብሰ ጸጋ አጥቶ ወደ ምድረ ፋይድ /የመከራ ቦታ/ ከተወረወረ በኋላ የደረሰበት የመጀመሪያ የመፍትሔ ሐሳብ ሳይለምነው የፈጠረውን ሳይጠይቅ የሰጠውን ፈጣሪውን በመሥጢረ ንስሐ አማካይነት ይቅርታ መጠየቅ ነበር ይህ መልካም ምኞቱም ተሳክቶለት አዳም የፈጸመውን በደል እያስታወሰ በአቀረበው የዕንባ፣ የኀዘን፣ የጸሎትና የጸጸት መስዋዕት እግዚአብሔር አምላኩን እስከ ቀራንዮ አደባባይ ድረስ በማምጣት ተባሮ ከወጣበት የክብር ሀገሩ ተመልሶ እንዲገባ በማድረግ የንስሐ መንፈሳዊ ጥቅም ተረጋግጧል።

ይህን ታላቅ መንፈሳዊ ኃይል የተረዳው ነቢዩ ኢዩኤልም ንስሐ ከእግዚአብሔር አምላካችን ጋር የምንገናኝበት ቸርነቱንም የምንናገርበት ሥርዓት መሆኑን ያስረዳል እንዲህ በማለት «አሁንስ ይላል እግዚአብሔር በፍጹም ልባችሁ በጾምም በልቅሶም ወደ እኔ ተመለሱ ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ አምላካችሁም እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ ቁጣው የዘገየ ምሕረቱም የበዛ ከክፉትም የተጸጸተ ነውና ወደ እርሱ ተመለሱ» ኢዮ.2÷12 በዚህ የጸጸት መንገድ ተጉዞ ነበር አዳም አምላኩ ጋር የተገናኘው።

ምክንያቱም አዳም የፈጸመው በደል፣ የደረሰበት ውድቀት ዲያብሎስ ከፈጸመው በደልና ከደረሰበት ውድቀት የሚያንስ ባይሆንም የፈጣሪውን ቸርነት በማመን ንስሐን ገንዘብ በማድረጉ የጠበቀውን ተስፋ ማግኘቱን ቅዱሳት መጽሐፍት ያበስሩናል።

ለ. <u>ሁለተኛው የንስሐ ሕይወት ተጠቃሚ ነቢዩ ዳዊት ነበር</u>

ነቢዩ ዳዊት ከቤተ እሥራኤል ነገሥት ሁሉ ታላቅና ተወዳጅ ሰው እንደነበር ዜና ታሪኩ ያስረዳል። ነገር ግን የሰው ልጅ እንዳኖሩት አይገኝምና በኃጢአት ወደቀ የበደሉ ዓይነትም ተደራራቢ ነበር ምክንያቱም የተወዳጅ ወታደሩ የኦርዮን ሚስት ጋር በዝሙት ከወደቀ በኋላ ይኸን የበደል ምሥጢር /ጉድ/ ለመደበቅ

ያስችለኛል ብሎ የገመተውን ሁሉ ቢያደርግም ሳያዋጣ በመቅረቱ ወታደሩን በግፍ እንዲገደል በማድረጉና ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ቤተ እሥራኤል እንዲቆጠሩ በማድረጉ እግዚአብሔርን አስቆጣ 2ሳሙ.11÷12 2ሳሙ.24

የሆነው ሁሉ ኀጢአት ለጊዜው ከሰዎች ይሰወር እንደሆነ እንጅ ጊዜውን ጠብቆ መገለጹ የማይቀር ቢሆንም ነቢዩ ናታንና በነቢዩ ጋድ የምክር አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆንና ንስሐ ለመግባት እንደ ልቤ የሚል የበረከት ስም ለማግኘት ችሏል።

የነቢዩ ዳዊት የንስሐ ጸሎም እንዲህ የሚል ነበር።
«እግዚአብሔርን ባደረግሁት ነገር እጅግ በድያለሁ፣ አሁን ግን አቤቱ ታላቅ ስንፍና አድርጌአለሁ የባሪያህን ኃጢአት ታርቅ ዘንድ እለምንሀለሁ። 2ሳሙ.24÷10

ታላቁ አባት ነቢዩ ዳዊት ከዙፋኑ ወርዶ ማቅ ለብሶ አመድ ነስንሶ፣ የንስሐ እንባውን በማፍሰስ በተሰበረ ልቡና በአቀረበው የይቅርታ ጥያቄ ያ ሁሉ በደል ተፍቆለት «እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም የሚያደርግ፣ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ» ተብሎ አምላካዊ ምስክርነት ለመስማት መብቃቱን ስናነብ ዛሬ በብዙ ምክንያቶች ተጠላልፈን ከእግዚአብሔር ተለይተን ለምንገኝ ወገኖች ምን ይሰማን ይሆን።

በብሉይ ኪዳን ከነበሩ አባቶች መካከል ለምሳሌ ያህል እነዚህን አነሳን እንጂ ሌሎችም የንስሐ ሕይወት ተጠቃሚ አባቶች በጣም ብዙ ናቸው ነገር ግን ሕይወታቸው ከሕይወታችን ጋር ሊመሳሰል የሚችልበትን ሁኔታ በማስታዋል በመረዳት ራሳችንን ለማዳን እንችል ዘንድ መንገድ ለማሳየት ያህል መጠቀሳቸውን ልናስተውል ይገባል።

ሐ. ንስሐ የመግባት ጥቅም በሐዲስ ኪዳን

የሐዲስ ኪዳን ምሥጢረ ንስሐ ከብሉይ ኪዳን በጣም የተለየ መሆኑን አስቀድሞ መረዳቱ ተገቢ ይመስለናል ምክንያቱም የብሉይ ኪዳን ንስሐ ለምድራዊ ለሥጋዊ ጥቅም ብቻ ማለትም ከረሀብ፣ ከጦርነት፣ ከስደት፣ ከመቅሰፍት ከተለያዩ ሥጋዊ መከራዎች ብቻ ለማዳን ካልሆነ በቀር

በበደል ምክንያት ወደ ተዘጋጀው ገነት የማስገባት ኃይል አልነበረውም የሐዲስ ኪዳን ምሥጢረ ንስሐ ግን ለገነት/መንግሥተ ሰማያት የሚያበቃ መሆኑ ተደጋግሞ ተገልጿል። «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» ተብሎ የመጀመሪያው አዋጅ የተነገረውም ለዚህ ነው። ሐዋርያው ቅ/ጴጥሮስም ስለ አዲስ ኪዳን ምሥጢረ ንስሐ አስፈላጊነት ሲያስረዳ እንዲህ ይላል «እንግዲህ ከጌታ ፊት የመጽናናት ዘመን እንዲመጣላችሁ ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም። የሐዋ.3÷19 በሐዲስ ኪዳን አንድ ሰው ኃጢአቱ በንስሐ ተደመሰሰለት ማለት ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀች ርስተ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ የተዘጋጀ መሆኑን ልብ ይሏል። ከዚህ በማያያዝ የሐዲስ ኪዳን ንስሐ ተጠቃሚዎችን እንመለከታለን።

መ. <u>ሐዋርያው ቅ/ጴጥሮስ</u>

ሐዋርያው ጴጥሮስ ከልማዳዊው ግብሩ አሣ አጥማጅነት ወደ ታላቅ ግብረ መንፈስ ቅዱስ ምእመናንን አጥማጅነት /ሰብሳቢነት/ በፈቃደ እግዚአብሔር ከጠራበት አንስቶ ብዙ ፈተናዎች ገጥመውታል ከነዚህም መካከል አስቸጋሪው ፈተና የገጠመው በሌሊተ ሐሙስ መድኃኒት ክርስቶስ በአይሁድ መካከል የማዳን ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ለቀረበለት ጥያቄ የሐሰት ምሥክርነት በመስጠቱና የሚያውቀውን ፈጣሪውን አላውቀውም ብሎ በመካዱ ነበር።

ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ እንደመዘገበው «ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ያለው ቃል ትዝ አለው ወደ ውጭም ወጥቶ መራር ልቅሶ አለቀሰ» ማቴ.26÷69‑75 ይላል።

ንስሐ ማስተዋልን ይጠይቃል ማስተዋል፣ የት እንደዋልን የት እንዳደርንም በየዕለቱ በየቦታው ምን እንደሠራን የሚገልጽልን መምህር ነው ሐዋርያው ቅ/ጴጥሮስ የዶሮውን መጮኽ ባያስተውል ንስሐ ሳልገባም ነበርና ስለማንነታችን ባስተዋልን ቁጥር ወደ ንስሐ ሕይወት እየቀረብን መሆኑን ልብ እንበል።

ሠ. <u>ፈያታዊ ዘየማን /ጥጦስ/</u>

ፈያታዊ ዘየማን እየተባለ የሚጠራው በጌታችን ከመስቀሉ በቀኝ በኩል የተሰቀለው ወንበዴ ሲሆን መላ ዘመኑን በገቢረ ኃጢአት ያጠናቀቀ እንደሆነ ሊቃውንት ይናገራሉ። ነገር ግን መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ መስቀል ላይ በዋለበት ወቅት እርሱም በቀኝ በኩል ተሰቅሎ ስለነበር የሄደበትን የበደል መንገድ በማስታወስ እንዲህ በማለት ኃጢአቱን አመነ «ስለ አደረግነውም የሚገባንን እንቀበላለንና በእኛስ እውነተኛ ፍርድ ነው ጌታ ሆይ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ።» በማለት ሲፈጽመው የነበረውን ኃጢአት አስታውሶ ይቅርታ መጠየቁን እናያለን ሉቃ.23÷41

በሐዲስ ኪዳንም ይሁን በብሉይ ኪዳን ለምሳሌ የቀረቡት አባቶች ሕይወታቸውን የተለየ የሚያደርገው የተሰጣቸውን የድኅነት ጊዜ ሳያባክኑ ራሳቸውን መርምረው የእግዚአብሔር የመንግሥቱ ወራሾች መሆናቸው ነው። የምሥጢረ ንስሐ ጥቅም የሚመዘነውም ከዚህ አንጻር መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ምክንያቱም ምሥጢራትን ሁሉ ለመፈጸም የሚያበቃው ሐብተ መንፈስ ቀዱስ የሚገኘው በንስሐ ስለሆነ ነው።

ለምሳሌ በሉቃስ ወንጌል ም.15 ታሪኩ የተመዘገበው የጠፋው ልጅ ወደ አባቱ ቤት ለመመለስ የቻለው ንስሐ ከገባ በኋላ መሆኑ ለዚህ አብነት ነው።

ከሰው ወገን ማንም ቢሆን ኃጢአት የለብኝም ብሎ እግዚአብሔርን መዋሸት የሚችልበት አንደበት የለውምና ከዓመት ዕቅዱ የመጀመሪያው ዕቅድ ንስሐ መግባት ቢሆን የተመረጠ ዕቅድ ይሆንለታል። «ኃጢአትን አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም» 1ዮሐ.1÷10 ኃጢአቱን አምኖ የሚጸጸት ሰው «አንተ አመፀኛ ከእኔ ራቅ የሚል የፍርድ ቃል አይሰማም ስለዚህም ብፁዕ ነው እንግዲህ ኃጢአት ማለት ሞት ስለሆነ ንስሐ ማለት ትንሣኤ ልቡና ማለት ነውና የሕያው እግዚአብሔር ልጆች እንባል ዘንድ እንዲሁም ይህ

ልጅ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኗል፤ ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም ለመባል እንበቃ ዘንድ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ።

2. በንስሐ ካለመመለስ የሚመጣ ቅጣት

የሰው ልጅ በጥንተ ተፈጥሮ በአርአያ እግዚአብሔር እንደተፈጠረና በሕያው እግዚአብሔር ሕይወትነት የከበረ ፍጡር እንደነበር መጻሕፍት ይመሰክራሉ። ዘፍ.2÷7

ነገር ግን ከጊዜ በኋላ የተሰጠውን አደራ በመዘንጋት በፈጸመው ስሕተት ከነበረበት የልዕልና ቦታ በመከራና በጭንቅ ወደሚኖርበት ዓለም ወረደ በነፍሱም ወደሲኦል ተጣለ።

ከዚያን ዘመን ጀምሮ ለእግዚአብሔር ቃል የማይታዘዙ የብዙ ሰዎች የሕይወት ታሪክ ተመዝግቦአል። በርካታ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እንደሚሉት «ክፉ ልብ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ አይጠቀምበትም። ወደ ቤተ እግዚአብሔር ይሔዳል ነገር ግን አይለወጥም። ክፉ ልብ የማይሰበር ዓለት የማይቀልጥ ብረት ነው» በማለት ይገልፁታል። ይህን አስመልክቶ ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ ለዕብራውያን ክርስቲያኖች ሲመክር

«ዛሬ ድምፁን ስትሰሙ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ» በማለት ለቃለ እግዚአብሔር ለምክረ ካህን፣ ለሥርዓተ ቤተክርስቲያን የምናሳየውን እልከኛነትና ደንታቢስነት በመረዳት ከሚመጣው ቁጣ መዳን የምንችልበትን መንገድ ያሳያል።

ሀ. በዚህ የእልከኝነት ገመድ ተጠላልፈው አምላካዊ ጥሪን ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ከምድራዊና ሰማያዊ በረከት ከተለዩት መካከል የመጀመሪያዎች በኖኅ ዘመን የነበሩ ሕዝቦች ናቸው። « እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸደ በልቡም አዘነ ዘፍ.6÷6» ተብሎ በወቅቱ የነበረው የኃጢአት ማዕበል ምድርን ያጥለቀለቀና ያበላሸ መሆኑ ተጽፏል።

ስለዚህ እግዚአብሔር ለምሕረቱና ለቸርነቱ ገደብ የለውም ሲባል እውነተኛ ፍርዱም የማይዛባ ስለሆነ በነዚህ ሕዝቦች ቅጣቱ ተላለፈ ምድር በንፍር ውኃ ተሞላች ከኖኅና ቤተሰቡ በስተቀር ሁሉም ተንቀሳቃሽ ከበደለኛው የሰው ልጅ ጋር በአንድነት ጠፉ።

በአመንዝራነት ርኩሰት የተበላሸችውን ምድር በምሥጢረ ንስሐ ያጸዱአት ዘንድ ጻድቁ ኖኅ አባታዊ ምክሩን አልነፈጋቸውም ነበር ነገር ግን የሚሰሙበት ጆሮ የሚያስተውሉበት ቅን ልቦና ከእነርሱ በመሰወሩ ሊቀበሉት አልቻሉም ቅጣቱም ተፈጸመባቸው ዘፍ.6÷1–7÷1–24

ለ. <u>ሰብአ ሰዶም ወገሞራ</u>

የፈለጉት ደስታ ሳይገኝ ያልፈለጉት ኃዘን ከተፍ ይላል እንደተባለው የአበው ቢሒል

- በሰዶምና ገሞራ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች የበደል ጩኸታቸው፣ እጅግ በመብዛቱ የኃጢአት ሸክማቸው እጅግ እየከበደ መምጣቱን እግዚአብሔር ተመለከተ ዘፍ.18÷20

- ሴቶችም ወንዶችም ለባሕሪያቸው የሚገባውን ሕገ ተፈጥሮ ለባሕሪያቸው በማይገባ እንስሳዊ ግብር መለወጣቸውን ተመለከተ ሮሜ.1÷26

- በመጨረሻም ምውት አዝሎ የሚዞር ሕያው በመጥፎ ዕድሉ ያፍርበታል እንደተባለው በሎጥ ቤት እንግድነትየተቀመጡ መላእክትን እንኳ ሳይፈሩና ሳያፍሩ የድፍረት ሙከራ ማድረጋቸውን ተመለከተ ይህን የተመለከተ እግዚአብሔርም በሶዶምና ገሞራ ላይ ከሰማይ እሳትና ዲን አዘነበ። እነዚያንም በከተሞች፣ ከተሞቹም የሚኖሩትን ሁሉ የምድሩንም ቡቃያ ሁሉ ገለበጠ እግዚአብሔርም እውነተኛ ፍርዱን ገለጠ ቀጣቸውም ዘፍ.19÷1–29

በመሠረቱ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ሳይመክርና ሳይዘክር የመዓት እጁን ያነሳበት ጊዜ የለምና ለነዚህ ሕዝቦችም የንስሐና የጽድቅ ምሣሌ የሆነ ሎጥን በመካከላቸው አስቀምጦ ነበር ማስተዋሉ የለምና አልተጠቀሙበትም እንጂ በዘመናችንም ቢሆን መልካም ከሚሠሩ ይልቅ ኃጢአትን የሚያዘወትሩ ሰዎች በብዛት የሚታዩ መሆናቸው ባይካድም ለአስተዋይ ሰው ግን የድኅነቱና የንስሐ ምሳሌ የሚሆኑ አባቶች ስለማይታጡ አስተውሎ መራመዱ ለንስሐ ያበቃል በወቅቱ መጠቀም ይቻላል «ኃጢአትህም እስከ ሰማይ እንዳይከተልህ ከዚሁ አስቀረው በደልህም ከዕለቱ ማስታወሻ ወደ ዋናው መዝገብ ተላልፎ እንዳይጻፍ ፀሐይ ሳይጠልቅ ሥርየት የምታገኝበትን መርምር በማለት በኃጢአት ምክንያት ከሚታዘዝ ቁጣ መዳን የሚቻለው በንስሐ መሆኑ የቅዱሳት መጻሕፍት የጋራ ምስክርነት ነው።

ሐ. <u>የግብፅ ንጉሥ ፈርኦን</u>

«እሥራኤልን አልለቅም እግዚአብሔርን አላውቅም» እያለ በኃይሉ ይመካ የነበረው ንጉሥ አወዳደቁ የሚያስደነግጥ፣ የሚያሳዝንም እንደሆነ የሕይወት ታሪኩ ይመሰክራል።

ቸርነቱ የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ እግዚአብሔር ፈርኦን ወደ ማስተዋልና ንስሐ ለመመለስ ይበቃ ዘንድ ያላደረገው የቸርነት ሥራ የለም የእግዚአብሔር የምሕረት እጁ በተዘረጋች ቁጥር የፈርኦን ልብ ጭካኔንና እልኸኝነትን እየተመላች ሄደች ከዚህ በኋላ ነበር የፈርኦን እልከኝነትና አለመመለስ በመከራ ሥጋና በመከራ ነፍስ የተደመደመው።

«ሙሴም እጁን በባሕሩ ላይ ዘረጋ÷ ባሕሩም ማለዳ ወደ መፍሰሱ ተመለሰ፣ ግብጻውያንም ከእርሱ ሸሹ እግዚአብሔርም ግብፃውያንን በባሕሩ መካከል ጣላቸው ውኃውም ወደ ባሕር የገቡትን ሰረገሎችን ፈረሰኞችንም የፈርኦንም ሠራዊት ሁሉ ከደነ ከእርሱም አንድ ስንኳ የቀረ የለም» ተብሎ የተጻፈው ታሪክ የሚገርመው የአንድ ሰው እልከኝነት ምንም የማያውቁ ወገኖችን የመከራው ተሳታፊ ማድረጉን ስንረዳ የበለጠ እንድንጠነቀቅ ያደርገናል ዘፀ.14÷26–29

«ፍራ እንጂ የትዕቢትን ነገር አታስብ ተብሎ የተጻፈውም ለዚህ ነው» ሮሜ.11÷20 የሆነ ሆኖ የዘመናት መራራቅ፣ የኃጢአት አፈጻጸም ልዩነት የበደል ግልፅነትና ስውርነት የማስተዋልና ያለማስተዋል ጥንቃቄ ጉድለት ካልሆነ በስተቀር ከሰው ወገን እግዚአብሔርን አልበደልኩም በማለት አፉን ሞልቶ መናገር የሚችል ሰው ያለ አይመስለኝም።

ምክንያቱም ከእውነት ይልቅ ሐሰትን፣ ከመስጠት ይለቅ መቀበልን፣ ከመጾም ይልቅ መመገብን፣ ከፍቅር ይልቅ ጥላቻን፣ ከርሕራሔ ይልቅ ጭካኔን ከማመን የልቅ ጥርጣሬን ከንጽሕ ቅድስና ይልቅ ርኩሰትን ምርጫው ያደረገ ግዙፍ ሥጋዊ ፈቃድን ለመንፈሳዊ ኃይል አስገዝቶ መገኘቱ ለብዙዎች ከባድ ሸክም መሆኑ ይታመናልና ነው።

ከዕለታት አንድ ቀን እግረ መንገዳችንን ወደ ቤተ እግዚአብሔር በመዝለቅ ከሰማናት ተባራሪ ቀለም /ትምህርት/ ባሻገር የእኛ ቸልተኝነት ተጨምሮ ይቅርና ይሁዳ የተባለው ደቀ መዝሙር መድኅን ክርስቶስ ከዋለበት እየዋለ ከአደረበት እያደረ የኃጢአትን አስከፊነት የንስሐን አስፈላጊነት በአግባቡ ተምሮ ነበር ነገር ግን በፍቅረ ንዋይ የታወረ ልቡናው አምላኩን እስከ መሸጥ አድርሶት በሁለት ሐሳብ እያነከሰ የንስሐ ዕድሉ ተሰጥቶት እያለ ሳይጠቀምበት በመቅረቱ ክርስቶስ በደሙ የከፈተለትን ሀገር ሳይወርስ ቀርቷል። የሐዋ.1÷16–19 ስለዚህ በታሪክ እንደተዘገበው ክፉ አወዳደቅ ላለመውደቅ እንዲህ ተመክረናል «እናንተ የእፉኝት ልጆች ከሚመጣው ቁጣ እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ» ሉቃ.3÷8 አዎ የሚመጣው ቁጣ ምንድን ነው ትለኝ እንደሆነ በምድራዊ መቅሰፍት መመታት፣ በመጨረሻው የፍርድ ቀን በግራ መቆም ነው። ማቴ.25÷32–33

ስለዚህ አሁን የምንመካበትና ተስፋ የምናደርገው ነገር ሁሉ እንዳልነበር ሆኖ እኛም በኃያሉ እግዚአብሔር ፊት በወቀሳ ቃል ተፈርዶብን ገሐነም ከመውረድ ለመዳን መፍትሔው በእጃችን መሆኑን መገንዘብ ያሻል። በሥጋ ፈቃድ እየተመሩ ለንስሐ ሕይወት ሳይበቁ አምላካዊ ቅጣት እንደተፈጸመባቸው ከተረዳን እኛም ብንሆን «እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞታላችሁ በመንፈስ ግን /በንስሐ/ የሰውነትን ሥራ /ኃጢአትን/ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ። ተብሎ በተጻፈው መሠረት ርስተ መንግሥተ ሰማያትን ከሚያሳጣ አምላካዊ ቁጣ ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል ሮሜ.8÷13

3. ንስሐ የምንገባው ለምንድን ነው?

ንስሐ በመግባት የተገኘውንና የሚገኘውን ጥቅም፣ ንስሐ ባለመግባት የተፈጸመውንና የሚፈጸመውን ቅጣት ቅዱሳት መጻሕፍትን መረጃ በማድረግ ተመልክተናል። የሁለቱንም ምሥጢር በምሳሌ ከተረዳን እኛስ የምንገባው ለምንድን ነው በማለት ስለ ምሥጢረ ንስሐ ዓላማ ልንገነዘበው የሚገባን ቁም ነገር አለ።

ወንጌላዊው ቅ/ዮሐንስ በራዕዩ «ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ ሥልጣን እንዲኖራቸው በደጆችዋም ወደ ከተማይቱ እዲገቡ ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብፁዓን ናቸው» በማለት በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ከተፈጸመ በደል መንፃትና መንግሥተ ሰማያት መግባት የሚቻለው በኃጢአት የጐሰቆለና ያደፈ ሰውነትን በንስሐ አንጽቶ አንደሆነና ይህን ሥርዓትም የፈጸሙ ብፁአን ተብለዋል።

ሥለዚህ ንስሐ የምንገባበት ምክንያት

ሀ. «ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሠረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ» ተብሎ በሐዋርያው ቅ/ጴጥሮስ በተነገረው መሠረት የሐዋ.2÷38 በተለያዩ ምክንያቶች ከጊዜ በኋላ ወደ ክርስትና ሕይወት ለሚመጡ ወገኖች በጥምቀት የእግዚአብሔር የጸጋ ልጆች ከመሆናቸው በፊት የሚቀድመው ንስሐ ስለሆነ።

ለ. ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም ለመቅረብ ንስሐ የመጀመሪያው ትእዛዝ ነው። የምሥጢረ ቁርባን ባለቤት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው ብሎ ሲያውጅ ደቀመዝሙሩ ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስም «ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት» በማለት ራሱን በንስሐ ሳይፈትን በደሉን ሳያስወግድ ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም መቅረብ የሚያስጠይቅ መሆኑን አስረድቶአል።

ስለዚህ ለቅዱስ ሥጋው ለክቡር ደሙ የሚያበቃን ቸርነቱን በማመን ንስሐ በመሆኑ

ሐ. ከሰማያዊና ምድራዊ ወቀሳ ለመዳን

እግዚአብሔር አምላካችን ካለንበት የኃጢአት ጉዞ ተመልሰን በሕይወት እንኖር ዘንድ ፈቃዱ ነው ስለሆነም በኀዘን ወይም በደስታ፣ በማግኘት፣ ወይም በማጣት፣ በመሸም ወይም በመሻር፣ በሕመም ወይም በጠ ኃንነት፣ በማየት ወይም በመስማት፣ ወዘተርፈ በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች የተስተካከለ የንስሐ ሕይወት እንዲኖረን ለማድረግ የቸርነት ሥራውን ከመሥራት ተቆጥቦ አያውቅም ነገር ግን የሰው ልጅ ሁሉንም የጥሪ መስመሮች አይቶ እንዳላየ ስለሚያልፋቸው ከወቀሳ አይድንም።

ለዚህም ነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ወዮልሽ ኮራዚን ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ በእናንተ የተደረገው ተአምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርጐ ቢሆን ኖሮ ማቅ ለብሰው አመድ ነስንሰው ከብዙ ጊዜ በፊት ንስሐ በገቡ ነበር» ተብሎ የወቀሳቸው እውነትም ዘወትር የእግዚአብሔርን ቃል እየሰማን ልባችን ደንድኖ ንስሐ ካልገባነው ይልቅ እስከ አሁን የእግዚአብሔርን ቃል ያልሰሙ ወገኖች ዕድሉ ደርሶአቸው ቃሉን ቢሰሙ ንስሐ በመግባት የሚቀድሙን መሆኑ አያጠራጥርም ማቴ.11÷21 እንዲህ ከሆነ ከሰማያዊና ምድራዊ ወቀሳ ለመዳን ንስሐ እንገባለን።

መ. ሰማያዊት ኢየሩሳሌምን ለመውረስ

የሰው ልጅ በሕይወቱ ብዙ ነገሮችን ይሰማል ለምሳሌ መዝሙር፣ ዘፈን ልቅሶ ወሬ ሐሜት ሌሎችን ማለት ቋንቋቸውን የሚያውቃቸውንም ይሁን የማያውቃቸውን ተንቀሳስቃሽ ነገሮችን ሁሉ ይሰማል እነዚህ

ሁሉ አልፌው የሚሰማው ቃል ግን ከነዚህ ሁሉ በእጅጉ የበለጠ ነው እርሱም «እናንተ የአባቴ ቡሩካን ወደ እኔ ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ» የሚል አምላካዊ ቃል ማቴ.25÷34 ያውም በዚህ ጊዜ ያልፋል /ይሻራል/የማይባል ዘለዓለማዊ መንግሥት ይችን ሐገር ለመውረስ ከእኛ የሚጠበቀው ንስሐ መሆኑ ብዙ መጽሐፍት አስረዱ በአጠቃላይ ሰው ከእግዚአብሔር የሚፈልገው ሰማያዊ ምድራዊ በረከት ለማግኘት ይችል ዘንድ ሁሉ ነገር ከእግዚአብሔር እንደሆነ አውቆ በንስሐ ከተስተካከለ ተስፋው ይለመልማል ምክንያቱም «ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል ተብሎ ተጽፎአልና» ማቴ.6÷33

4. ንስሐ ስለመግባት የሚቀርቡ ምክንያቶች

ብዙ ሰዎች ብዙ የስሕተት ምክንያቶችን አቅርበው ነበር ከፍርድ ግን አላመለጡም ለምሳሌ የመጀመሪያው ሰው አዳም ሔዋን አሳተችኝ፣ ሔዋንም እባብ አሳተችኝ በማለት አሳማኝ ነው የተባለ ምክንያት ቢቀርብም ከንጉሡ ሰማያት ወምድር እግዚአብሔር የተሰጠው መልስ ግን ከኔ ይልቅ የሌሎችን ሰምታችኋልና ርጉማን ሁኑ የሚል እንደነበር እናውቃለን ዘፍ.3÷17 ባለንበት ዘመንም ቢሆን ከዚህ የተለየ ነገር አይስተዋልም የንስሐ ጉዳይ ሲነሳ የምክንያቶችን ብዛት ኃጢአትን የሚሸፍኑ ይመስለናል ነገር ግን አይቻልም ምክንያቱም ጠላት ዲያብሎስ የክርስቲያኖችን ሕይወት ለማጥፋት የገነባውንየኃጢአት ሕንፃ ሁሉ በእግዚአብሔር ቸርነት ስለሚንድበት የንስሐ ጊዜ በየምክንያቶቹ እንዲዘገይ የሚያደርግ መሆኑ ሊታወቅ ይገባዋል፡ <u>እስኪ ከሚቀርቡት ምክንያቶች ጥቂቶቹን እንጥቀስ</u>

ሀ. የፈጸምኩት ስሕተት የለም በማለት ራስን ማሳመን አንድ ሰው ይህን ለማለት የሚያበቃው ከእርሱ የበለጠ ሌላ ኃጢአተኛ አለ ብሎ በመገመቱ ሲሆን ነገር ግን የሌሎችን እንጂ የራሱን ባለማየቱ የመጣበት ችግር ነው ከእርሱ የበለጠ ኃጢአተኛ መኖሩን ቢያረጋግጥ እንኳን «ይህን ዓለም አትምሰሉ ተብሎ የተጻፈውን መመልከት ለንስሐ ያበቃል» ሮሜ.12÷2

ለ. ደካማ በመሆኔ ትእዛዛትን መሸከም አልችልም

- እግዚአብሔር በሕይወቱ ሁሉ የተለየው ሰው እውነትም ደካማ ነው።
- እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የሆነ ሰው ግን ምን ጊዜም ብርቱና የጸና ነው።

ምክንያቱም ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ «ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ» በማለት ማንኛውም መንፈሳዊ ሥራ የሚሠራው በእግዚአብሔር ቸርነት እንጂ በሰዎች ሥጋዊ ኃይል አለመሆኑን ዐውቆ እግዚአብሔርን አጋዥ አድርጎ ወደ ንስሐ መቅረብ ሸክሙን ያቀለዋል «እናንተ ሸክማችሁ የከበደ ወደ እኔ ኑ የተባለው ለእኛ ነውና» ማቴ.11÷28

ሐ. የአካባቢ ተጽእኖ አለብኝ

ምእመኑ ያለበት አካባቢ የቤተ ክርስቲያን ርቀት፣ የካህናት እጥረት የሥራ ብዛት የጓደኝነት ችግር የመሳሰሉት የንስሐ ሕይወቱን የሚያጨልሙ ሆነው ሊታዩት ይችላሉ ነገር ግን አንድ ክርስቲያን ይህን አይነት ችግር ተቋቁሞ ወደ ንስሐ መምጣት ሲችል ነው እውነትም ክርስቲያን የሚሰኘው ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ ከላይ በተገለጸው ችግር ውስጥ የሚገኙ ምእመናንን ሲመክርና ሲያጽናና «እንገፋለን እንጂ አንጨነቅም፣ እንወድቃለን እንጂ አንጠፋም» በማለት ተስፋውን በእግዚአብሔር ላይ አድርጎ ወደ እግዚአብሔር በንስሐ ለመቅረብ ጥረት የሚያደርግ ምእመን ጥረቱ የሚሳካለት መሆኑን ያስተምራል።

መ. ተመልሼ ወደ ኃጢአት እገባለሁ

ንስሐ ኃጢአትን ለመደምሰስ በክርስትና ሕይወት ውስጥ አስፈላጊና ዓይነተኛ መፍትሔ መሆኑ የታመነ ነው። ነገር ግን አንዳንድ ምእመናን የመጀመሪያውን ኃጢአት በንስሐ አስወግዶ ሁለተኛ በደል አለመፈጸም በጸሎት መትጋት ሲገባ ገና ለገና ድጋሚ ኃጢአት ልሠራ ስለምችል ባለሁበት እየረገጥሁ መቆየት አለብኝ ማለቱ ሁለተኛ በደል ነው።

ምክንያቱም በኃጢአት ጸንቶ የሚኖር ሰው «ደመወዙ ሞት» መሆኑ ሊታወቅ የሚገባ ነገር ነው። ያዕ.1÷15 ኃጢአት የሥጋም የመንፈስም ሞት ነውና።

የእድሜ ወሰናችን የት እንደሚያደርሰን በማናውቅበት መንገድ ላይ በቀን ነገ የምንሠራውን ኃጢአት በማሰብ የዛሬውን መልካም የንስሐ ዕድል እንደዋዛ ብናልፈው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል» ብሎ የተናገረው ቃል በዚህ ላይ ይፈጸማልማቴ.7÷18 በአጠቃላይ ግን «ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል» መባሉ የነገን ሲያስቡ አለመድረስ አለና ለንስሐ እንፍጠን ማቴ.16÷26

5. ንስሐ የምንገባበት ጊዜ

ንስሐ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ነው ቢባል ተጋነነ አይባለም። የሰው ልጅ ከመዐልቱ ወይም ከሌሊቱ በየትኛው ክፍለ ጊዜ ወደ ፈጣሪው እንደሚጠራ የሚያውቅበት ጥበብ አልተሰጠውም ነገር ግን ማወቅ የሚችለውን ያህል ዕውቀት ተሰጥቷል። እርሱም ምንጊዜም ተጠንቅቆ መኖር ነው። በማቴዎስ ወንጌል 24÷43የእውቀቱ መግለጫ እንዲህ ይላል «ያን ግን እወቁ ባለቤት ከሌሊቱ በየትኛው ክፍል ሌባ እንደሚመጣ ቢያውቅ ኖሮ÷በነቃ ቤቱም ሊቆፈር ባልቻለም ነበር። ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ÷ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና»

በመሠረቱ የሰው ሕይወት ብዙ ጊዜ የሚያስበው መኖርን ብቻ ስለሆነ ንስሐን በወቅቱ ሳይጠቀምበት ጥሪ ይደርሰዋል አወዳደቁም የከፋ ይሆናል እርሱም በገሐነም።

ንስሐ ጊዜ የማይሰጠው አፋጣኝ ሥራ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ይገልጻሉ በምሣሌነትም ጻድቁ ኖኅ በወቅቱ መርከብን ባይሠራ ዕብ.11÷7 ንጉሥ ሕዝቅያስ ወቅቱን የጠበቀ ንስሐ ባይገባ 2ነገ.20÷1–7

ሐዋርያው ቅ/ጴጥሮስ በበደለበት ቀን የንስሐ ልቅሶ ባያፈስ ማቴ.26÷29 ታሪካቸው በመለኮታዊ ቅጣት ከተቀጡት ታሪክ የተለየ ባልሆነ ነበር።

ሥለዚህ የመዳን ቀን ነገ ሳይሆን ዛሬ ነው የሰው ልጅ ክርስቶስ የሚመጣውም ነገ ሳይሆን ዛሬ ነው ንስሐ የምንገባበት ዕለት ሰዓቱም ዛሬ /አሁን/ መሆኑን እንገንዘብ

6. ንስሐን ለማን እንናዘዝ

በመግቢያችን ላይ ንስሐ ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን አንዱ መሆኑን መግለጻችን ይታወሳል። ይህም ማለት ምሥጢራት የሚፈጸሙት ደግሞ በካህናት አባቶች ብቻ መሆናቸው ግድ ነው።

ከዚያ በፊት ግን ንስሐ ለመግባት አስቀድሞ የራስ ፈቃደኝነት ያስፈልጋል የራስ ፈቃደኝነት ካለ አሁን ያለበትን የኃጢአት ባሕር የጥፋት አዘቅት ይገነዘባል በዚህም ምክንያት ህሊናው ተነሳስቶ ወደ አባቶች ለመቅረብ ጊዜ አይወስድበትም ይህም ብቻ አይደለም ኃጢአቱን አምኖ ወደ መምህረ ንስሐው የቀረበ ምእመን ያለምንም መደበቅ ንስሐውን ለካህኑ ለመንገርና ከአምላኩ የሚታረቅበት ቀንም በጉጉት ይጠብቃል።

በቅድስት ቤተክርስቲያናችን ሥርዓት መሠረት ማንኛውም ምእመን የሚያከናውናቸው ሃይማኖታዊ መንፈሳዊ ክንዋኔዎች በመምህረ ንስሐው አማካኝነት መመሪያ እየተሰጣቸው የሚፈጽሙና የሚከናወኑ ናቸው። ምሥጢረ ንስሐ ሲባል ኑዛዜም የግድ ነው።

ኑዛዜ ማለት ሲሠራ ያላፈረውን ኃጢአት ሲናገር ሳያፍር ለካህኑ መናገር፣ መዘርዘር፣ ልቡናውን ታዛቢ ምስክር፣ አንደበቱን ከሳሽ እግዚአብሔርን ዳኛ አድርጐ ራሱን መክሰስ ማለት ነው ምክንያቱም ያለ ኑዛኔ ንስሐ ያለ ንስሐ ኑዛዜ የለምና ነው።

ካህኑም ንስሐውን ተመልክቶ ኑዛዜውን ሰምቶ በሰፊሐ እድ በሰቂሰ አእይንት በአንቃዕድዎ ሕሊና የንስሐን ጸሎት ያደርግለታል። የንስሐ አፈጻጸም መመሪያም ይሰጠዋል።ምክንያቱም ንስሐ ዘማዊውን እንደ ድንግል፣ ኃጢአተኛውን እንደ ጻድቅ ያደርገዋል። ተብሎ ተጽፏልና።

7. ከኑዛዜ በኋላ የሚሰጡ ቅጣቶች

ካህኑ የተነሳሒውን ኑዛዜ ከአዳመጠና ከተቀበለ በኋላ የሚከተሉትን የንስሐ ቅጣቶች በተወሰኑ ቀናት፣ ወራት፣ ሳምንታት ይፈጽም ዘንድ ያዘዋል።

በጸሎት መትጋት፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ፣ ከንብረቱ ለነዳያን ምፅዋት መስጠት/አስተብርኮ/ ስግደት መያዝ፣ አብዝቶ ከመብላትና መጠጣት መቆጠብ አብዝቶ ከመናገርም እንደዚሁ። ይህም የሚሆንበት ምክንያት ውኃ የደፈውን ልብስና የሰውን አካል እንደሚያነፃ ያስረጀውን ልብስ እንደሚያድስ ንስሐም የጐሰቆለውን ሰውነት ያረጀውን ሕይወት ያድሳልና ንስሐ የማይገባ ሰው ክርስትናው ከንቱ ነው በደሉ የበዛ ይሆናልና ንስሐ የሚገባ ራሱንም ለመምህረ ንስሐው የሚያስመረምር ሰው ሁልጊዜ ሕይወቱ የተጠበቀ ነው።

በአጠቃላይ ንስሐ በኑዛዜ ተጀምሮ በሥጋወደሙ የሚጠናቀቅ ስለሆነ የአባቶች ካህናት ድርሻ በምእመናን ሕይወት ውስጥ የጐላ ድርሻ አለው ወደ ንስሐ ሕይወት የሚመጣው ምእመን ከቤተ ክርስቲያንና ከካህናት በቀር የተሻለ መንፈሳዊ ሕይወት ሊያገኝበት የሚችሉበት ቦታ የለም ስለዚህ ማንኛውም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምእመን በሚያደርጋቸው ሥጋዊና መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ከካህናት አባቶች ሳይደበቅ በምክራቸውእየተጠቀሙ መኳዝ ይኖርበታል ከመሰናከል ለኃጢአት ከመዝት ያድናልና።

8. ምሥጢረ ንስሐና የካህኑ ሥልጣን

በነቢያትና ሐዋርያት መሠረት ላይ የተመሠረተችው ቅድስት ቤተክርስቲያን መመሪያዋ መጽሐፍ ቅዱስ እንደመሆኑ መጠን በምሥጢረ ንስሐ በኩል አልፈው ምእመናን መንግሥተ ሰማያት ይገቡ ዘንድ ታላቅ ሥልጣን የተሰጠው ለአባቶች ካህናት እንደሆነ ከባለቤቱ ክርስቶስ እንማራለን።

«የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻ እሰጥሀለሁ በምድር ያሰርኸው በሰማያት የታሰረ ነው በምድር የፈታኸው በሰማያትም የተፈታ ነው» ማቴ.16÷18 በዚህ አምላካዊ ቃል መሠረት ወደ መንግሥተ ሰማያት ለማስገባት ከመንግሥተ ሰማያት ለማስወጣት ይችሉ ዘንድ ለአባቶች ካህናት ሥልጣን መሰጠቱ ንስሐና ማንኛውም መንፈሳዊ ሥርዓት ተጀምሮ የሚያልቀው በካህናት አባቶች መሆኑ አያከራክርም።

ስለዚህ «ስለሕጉ ካህናቱን ጠይቅ» ሐጌ.2÷11 በተባለው መሠረት ምእመናን በሁሉም ምድራዊና ሰማያዊ፣ /ሥጋዊና መንፈሳዊ/ እንቅስቃሴያቸውን ከአባቶች ባለመደበቅ ምክር እየተቀበሉ ሕይወታቸውን ቢመሩ ከክፉ አወዳደቅ ይጠበቃሉ ቢሰናከሉም ትንሣኤ ልቡና ለማግኘት ጊዜ አይወስድባቸውም።

<u>ማጠቃለያ</u>

በንስሐ ውስጥ የሚያልፍ ተነሳሒ ከሚጠበቁበት መንፈሳዊ ግዴታዎች መካከል

1. ኃጢአተኛነቱን ማመን፣
2. ኃጢአትን መጥላት
3. በእግዚአብሔር ፊት ማልቀስ
4. ከንስሐ አባቱ ቀርቦ ከልብ እያለቀሰ መናዘዝ
5. የበደለውን መካስ
6. ለኃጢአተኞች ማዘንና መጸለይ በየጊዜው ከኃጢአት መጠበቅ የዘወትር ተግባሩ ሊሆን ያስፈልጋል እነዚህን የጠበቀ ተነሳሒ በሕይወቱ የንስሐ ፍሬ ይታይበታል እነርሱም ፍቅር፣ ሰላም፣ ትዕግሥት ቸርነት በጎነት የውስት፣ ራስን መግዛት የመሳሰሉት ናቸው።

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን